“በአባቶችሽ ፈንታ ልጆች ተወለዱልሽ በምድርም ሁሉ ላይ ገዥዎች አድርገሽ ትሾሚያቸዋለሽ ለልጅ ልጅ ሁሉ ስምሽን ያሳስባሉ።
መዝ 44(45)16-17

## መንፈሳዊ ቅናት

ስሟን እየጠሩ
ሲያመሰግኑ ሲዘምሩ
ለነዳያን ሲዘክሩ
በፆም በፀሎት በሰባኤ
በአማላጅነቷ እየተማፀኑ
በረከትን ሲቀበሉ
የዕድሜ ፀጋ ተሰጥቷቸው
አክሊሉ ተዘጋጅቶ
ቤታቸው ሞልቶ
ሀዘን ጠፍቶ
በደስታ ተተክቶ
አንገትን ሳያስደፉ
የሚያኖር በዕፁብ ተስፋ
የእምነታቸው መአዛ
ትውፊት ጌጥ መለያቸው
መሠረተ- ሃይማኖት ቋንቋቸው
የገድል የትሩፋት መነሻቸው
ዕውን ራዕይ ትንቢታቸው
ንፁህ ዘር መገኛቸው
በስደት ሀገር ጣዕማቸው
ከአባቶች የተረከብናት
ምሳሌ የማይገኝላት
ብርቅ ዕንቁ አለኝታችን
የምስራቅ በር እመቤታችን
ዛሬም ይኸው በዝማሬ
አጣፍጬ መናገሬ
እንደ አባቴ እንደ ዳዊት
በገናውና መደርደሬ
ዮሐንስ ፍቁረ-እግዚእን
የመስቀሉ እግር ስር ባለውለታ
ማስታወሴ መዘከሬ
እንዲያስተምረኝ መስተንግዶ
ትህትናን አለማምዶ
ለመታዘዝ አደግድጎ
እመቤቴን ልቤ ወድዶ
የሷ እንድሆን ለዘለዓለም
ሮጬ አምልጬ ከዚህ ዓለም
በንስሃ ዛሬም ነገም።

ከኃይለመሰቀልተስፋዬ
ለንደን